# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪ መፅሐፍ

## አንደኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

ግብረ ገብ ትምህርት የተማሪ መፅሐፍ አንደኛ ክፍል

የግብረ ገብ ትምህርት

የተማሪ መፅሐፍ

አንደኛ ክፍል



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪ መፅሐፍ

## የ1ኛ ክፍል


አዘጋጆች:- ትዛዙ ሙሐመድ (M.A)
ዘውዱ ተምትም (M.A)

አርታኢዎች:-አለማየሁ ነጋሽ (PHD)
ቃለወንጌል ምንአለ(PHD)
ሙሉጌታ ያየህ (PHD)

ሰዓሊ ኤልዛልሞን ጌቱ

ሌይአውት ዲዛይነር ኃይለጊዮርጊስ ተመስገን (አስማምቶ የሰራው)
ናትናዔል ውበሸት

ተርጓሚዎች ምስጋናው በቀለ(M.A)
ወልዴ በርሄ (M.A)

አርታኢና ገምጋሚ ምህረቱ ዋሌ(M.A)

አስተባባሪ ጌታቸው ታለማ(M.A)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

መጀመርያ የታተመው በ 2022 እ.አ.አ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የትምህርት ጥራትና ማሻሻያ መረሃ-ግብር ለፍትሃዊነት (GEQIP-E)፤በአለም ባንክ የሚደገፈው የእንግሊዝ አለም አቀፍ ዲፓርትመንት አሁን ከውጭ የጋራ ሀብትና ልማት ቢሮ ጋር የተቀላቀለው /DFID-, የፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሮያል የኖርወይ ኢምባሲ፤ የተባብሩት መንግስታት ህጻናት ፈንድ /UNICEF)፡ አለም አቀፍ የትምህርት አጋርነትና የዴንማርክ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር (GPE)፤ እና በብዙ ለጋሽ (ትረስትፈንድ) በኩል ነው።

© 2022 መብቱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የተረጋገጠ ነው፡ ፡ የጸሀፊው የሞራል መብቶች ተረጋግጧል። ከዚህ የመምህሩ መማሪያ መጽሐፍ ክፍል አስቀድሞ ከትምህርት ሚኒስቴር የጽሁፍ ፍቃድ ወይም ፍቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በማንኛውም መልኩ በኤሌክትሮኒክስ፣ ሜካኒካል፣ ማግኔቲክ፣ ፎቶ ኮፒ፣ ቅጂ ወይም በሌላ መልኩ ተባዝቶ ማስተላለፍ አይቻልም። ይህም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የቅጂ መብትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ታውጇል።

የትምህርት ሚኒስቴር ይህንን የመምህሩ መማርያ መጽሐፍ ለማሳተም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳተፉትን በርካታ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን እና ሌሎች አካላትን ማመስገን ይፈልጋል። ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ እና ጅማ ዩኒቨርስቲ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ልዩ ምስጋና ይገባቸዋል።

በባለቤቶቻቸው ፈቃድ ጥቅም ላይ የዋሉ የቅጂ መብት ያላቸው ቁሳቁሶች ናቸው። በቅጂ መብት የተጠበቁ ነገሮች ያልተጠቀሱ ወይም ያለአግባብ ያልተጠቀሱ ከሆነ እባኮትን የትምህርት ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤት አራት ኪሎ (ፖ.ሳ.ቁ 1367) ፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ያነጋግሩ።

የታተመው:

xxxxxxxx

ፖ.ሳ.ቁ xxxxxx

ኢትዮጵያ

በትምህርት ሚኒስተር ስር ስምምነት ቁ. xxxxxxxxxxx

ISBN: 978-999944-2-046-9

# ይህ መጽሐፍ በጥንቃቄ ይያዝ!




ይህ የመማሪያ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው፡፡ ስለዚህም እንዳይጎዳ ወይም እንዳይጠፋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጉ፡፡ መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ይረዷችሁ ዘንድ የሚከተሉትን10 ነጥቦች አስተውሉ

1. መጽሐፉንእንደፕላስቲክ፣ጋዜጣ እና በመሳሰሉ ቁሶች መሸፈን፣
2. መጽሐፉን ንጹህ እና ደረቅ ቦታ ማስቀመጥ፣
3. መጽሐፉን በሚጠቀሙበት ጊዜ እጅዎት ንጹህ መሆኑን ማረጋገጥ
4. በመጽሐ ፉሽፋኑም ሆነ የውስጥ ገጾች ላይ አለ መጻፍ፣
5. ገጾችን ከማጠፍ ይልቅ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድ ለምልክት መጠቀም፣
6. ማናቸውንም ምስሎች ወይም ገጾችን ፈጽሞ አለመቅደድ
7. ማናቸውንም የተቀደዱ ገጾች መጠገን፣
8. መጽሐፉን በቦርሳ ውስጥ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፣
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ሲያውሱ በጥንቃቄ ማቀበል፣
10. አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቀሙ፤መጽሐፉን በጀርባ ሽፋኑ በኩል ማስቀመጥ ከዚያም በአንድ ጊዜ ውስ ንገጾችን መግለጽ፤ እንዲሁም የመጽሐፉን ጠርዞች በትንሹ ጫንጫን

# መግቢያ

የሰው ልጅ ምክንያታዊ ፍጡር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሰው ልጆች ከሌሎች ፍጥረታት የሚለዩት በባህሪ ነው፡፡ይህም ለሰው ልጆች ብቻ የተሰጠ ፀጋ ነው።ባህሪ የሚገነባው የሰው ልጆች ያለሙትን ዓላማ ለማሳካት በሚያደርጉት ጥረት ነው። የተሻለ ባህሪ ለመያዝ ሰዎች ምክንያትን፣ መርህን እና ግብረ-ገብን መሰረትማድረግ ይገባቸዋል። ባህሪ የአንድን አካል ድርጊት በመኮረጅ የሚገነባ ሳይሆን በግል አስተሳሰብና ጥረት የሚሆን ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ ከሌሎች የምድር ፍጥረታት የሚለየው በምክንያት እና በህሊና የሚመራ በመሆኑ ነው። ይህ መሰረታዊ ሁኔታ የሰው ልጅ ባህሪእንዲያዳብርና ለሌሎች የሰው ዘሮች መመርያን፣ ስልጠናን እና ትምህርትን በመስጠት በህይወትእንዲቆዩ አስችሏል። የሰው ልጅ ባህሪ እና ችሎታ በተፈጥሮ የማይገኝ በመሆኑ በትምህርት እና ስልጠና ይዳብራል። ስለዚህ በትምህርት እና ስልጠና የምናዳብርው ባህሪየተለየ እና በእጅግ አስፈላጊ መሆኑ ተገቢ ነው። ይህም ባህሪ የወደፊት ግብን እና ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ እና በግብረገብ የታነፀስብዕና የሚያስገኝ ነው። ምንም እንኳን የሰው ልጅ በተለያዩ ማህብራዊ ግንኙነት የሚኖር ቢሆንም የላቀ ግብረገብ ስብዕና እንዲኖረው በትምህርት መደገፍ ይኖርብታል።

መልካምነት በተፈጥሮ የማይገኝ ፀጋ በመሆኑ በድግግሞሽ እና በትምህርት በማዳበር ቀናነትን እና በግብረ-ገብ የታነፀ ዜጋ መፍጠር ይቻላል። የሰው ልጅ ማህበራዊ ህይወት በግብረ-ገብ የሚመራ በመሆኑ የዕለት ተዕለት መሠረታዊ ክንዋኔዎች ግብረ-ገብንማዕከል ያደርጋል።አንድ ሰው ብቻውን የሰው ልጅ ባህሪ ሊላበስ ስለማይችል በአካባቢው የሚገኝ የማሕበረሰብ አካልን መሰረት ማድረግ ይገባዋል። ለምሳሌ አንድ ሰው ብቻ በምድር የሚኖር ቢሆን ግብረ-ገብነት ላያስፈልገው ይችላል። ስለዚህ ግለሰብና በዙርያው የሚገኘውማህበረሰብ ሁለት የማይነጣጠሉ አካላት ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ግብረ-ገብ ማለት እውነትን መረዳትና በዚህ ውስብስብ ዓለም የመኖር ስልትን መገንዘብንያስረዳል። አንድ ማህበረሰብ ልክ፣ ስህተት እና ተገቢ ናቸው የሚባሉ ባህርያትን ይወስናል። ስለዚህ እነዚህ መርሆዎች እና መመርያዎች ማህበረሰቡ የዕለትተዕለት ክንዋኔዎችን በተገቢው ሁኔታ እንዲተገብር ይረዱታል። አንድ ማህበረሰብ እንደማህበረሰብ ይቀጥል ዘንድ ማህበራዊ ደንቦቹንናልማዱን ለየትውልዱ ማውረስ ያስፈለገዋል።

ሰዎች ስለማህበረሰብ ደንቦችናልማዶች ካልተማሩ የደንብ እና ልማድ መተላለፍ ሊኖር ይችላል። ታዳጊዎችን ስለማሕበረሰብ ደንብ እና ልማድ በተገቢው ሁኔታ ማስተማር ከስህተትና ከጥፋት ያድናቸዋል። ሰዎች የማሕበረስብ ወግና ልማድ የሚማሩት በአስገዳጅ ግብረ-ገብ ክንዋኔዎች ነው፡፡ ይህም ማለትማህበረሰቡ ልማድ እና ግብረ-ገብ ወጎቹንበማክበርያጎለብታል፤እንዲሁም የሰዎች የዕለትተዕለት ክንውንና ልማድ ሲሆን እንደማህበረሰብ መመርያ ያገለግላል። ስለዚህ ምን ማድረግ እንዳለብንና ምን መተው እንዳለብን ይጠቁማል።

ግብረ-ገብነት በተለያዩደንቦች የታቀፈ ሲሆን እያንዳንዱ ግለሰብ ከአከበራቸው ሁሉም ሰው ተጠቃሚ ይሆናል። እያንዳንዱ ሰው ለእነዚህ ደንቦች መገዛት ይኖርበታል፤ምንም እንኳን ነፃነቱን ቢገድቡም። ግብረ-ገብ የሚከተሉት አምስት ጠቀሜታዎች አሉት። 1. ማህበረሰብን ከውድቀት ለመከላከል፤ 2.የሰዎችን ስቃይ ለመቀነስ፤ 3.ሰዋዊ ማንነትን ለማንፀባረቅ፤ 4.ግጭትና አለመግባባቶችን በፍትሕና በደንብ ለመፍታት፤ 5. ምስጋናን ከወቀሳ፣ ሽልማትን ከቅጣት እንዲሁም ከጥፋተኝነት አንፃር ለመወሰን። ግብረ-ገብ ከጥንቃቄ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ጥንቃቄ ከማህበረሰብ መለኪያ አንፃርደንቦችንና ህግጋትንበመያዝየጋራግብንለማሳካት ይረዳል።በዘመናችን የግብረ-ገብ ትምህርት ለሰው ልጅ ህልውና እና ዕድገት የላቀ ሚና አለው።

በዘመናችን የግብረ-ገብ ትምህርት ለሰው ልጆች የመኖር ህልውና እና እድገት የላቀ ሚና አለው። እንደአንድ ነፃ እና የሰለጠነ ማህበረሰብ ለመቀጠል ለግብረ-ገብ እሴቶች ከቀደመው ወቅት በተሻለ ሁኔታ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ሰዎች የግብረ-ገብ ደንቦችና መርሆች ቢኖራቸውም ለትግበራቸው ቁርጠኝነት ከሌለ የተሻለ ባህሪ እና ግብረ-ገብነትን ለመፍጠር ዋስትና ሊሆኑ አይችሉም።የግብረ-ገብ እሴቶች በሰዎች የዕለትተዕለት ተግባራት አብሮነትን በመፍጠር የመኖር ህልውናን ያሰፍናሉ። ይሁን እንጂ የግብረ-ገብ እሴቶች በሚፈለገው ልክ ያልዳበሩ በመሆኑ የሰው ልጅ በሌላው ላይ አጥፊ ድርጊትን ከመፈፀም አላገደውም። ስለዚህ የግብረ-ገብ ትምህርት አስፈላጊነት በዚህ ዘመን ከፍ ያለ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የግብረ-ገብ እሴቶችንና ደረጃዎችን ለማስረፅ፡ ኢሰብአዊ ድረጊቶችን፣ መከራን እና ግፍን ከመቀነስና ከማጥፋት አንፃር ይህ ትምህርት የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የግብረ-ገብ ትምህርት መሰረታዊ ዓላማ ታማኝነትን፣ ራስን መግዛትን፣ ጉብዝናን፣ ወንድማማችነትን፣ ትህትናን፣ ክብርን እና መቻቻልን እንደ ህግና ደንብ ማስተማርንና ማዳበርን ይመለከታል።

የግብረ-ገብ ትምህርትታዳጊዎች እነዚህን ፀጋዎችንና የግብረ-ገብ ባህርያትን በመላበስ የተሻለ ህይወት እንዲኖሩ፣ ከብጥብጥ የፀዳ ሰለማዊ ግንኙነት እንዲፈጥሩና ውጤታማ እነዲሆኑ ይረዳል። ይህ ተማሪዎች የጋራ ዓላማ እና ሰለማዊ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ይጠቅማቸዋል። ይህ ማለት የግብረ-ገብ ትምህርት ለተማሪዎች የስብዕና ግንባታ እናለወደፊት ህይወታቸውስኬት የላቀ ጠቀሜታ አለው።

የግብረ-ገብ ትምህርት ማህበረሰቡ የተቀበላቸውን እሴቶችን እና ወጎችን ለተማሪዎች ለማድረስ ይረዳል። ግብረ-ገብን ማዳበር ማለትደንብና መልካም እሴቶችን ማተም ሳይሆን በሂደት የሚዳብር የግንዛቤ መዋቅርን የሚያሻሽል ተግባር ነው። የግብረ-ገብ ትምህርት በጥልቅ ማሰብን፤ ብቃት ያለው ውሳኔ መስጠትን እና በስነ-ምግባር ማስረዳትን በማላበስ የተማሪዎችን አዕምሮአዊ ክህሎትን ያሳድጋል። ከዚህ በተጨማሪ ጥልቅ ስሜትን እንደ ሩህሩህነት፣ ለሌላው ማሰብን፣ ታማኝነትን፣ አክባሪነትን፣ ሃላፊነትን መሸከም እና ፍትሐዊነትን ለማስተማር ይረዳል። በአጠቃላይ የግብረ-ገብ ትምህርት ግብረገብን በማጎልበትናስነ-ምግባርን በማላበስ የማህበረሰብ ህይወት የተሻለ እንዲሆን ይጠቅማል።

በኢትዮጵያ የግብረ-ገብ ትምህርት አዲስ ክስተት አይደለም። ምክንያቱም በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ይሰጥ ነበር፤ ምንም እንኳን የትምህርቱ ይዘት በወቅቱ ለነበረው መንግስት ያደላ ቢሆንም። ይህ አዲሱ የግብረ-ገብትምህርት በዋነኝነት ዓላማ ያደረገው የተማሪዎችን የባህሪና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ላይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ስርዓተ ትምህርቱ ሃላፊነት የሚሰማው ዜጋን መፍጠርን ታሳቢ አድርጓል። ትምህርቱከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብና ከአዲሱ የስርዓተ ትምህርት ፍኖታ ካርታ ጋር በማስማማት እንደአንድ የትምህርት ዓይነት ከ1ኛ-6ኛ ክፍል እንዲሰጥ ተዘጋጅቷል።የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን አካቶ ይዟል፡- ስነ ስርዓትን ማክበር፣የሰው ልጅን ማክበር፣ ራስን ማነፅን፣ የግብረ-ገብ ሃላፊነትን በተገቢው ሁኔታ መወጣትን፣ የታዳጊዎች ስነ-ስርዓት፣ እውነትንና ታማኝነትን መሻት፣ አብሮነት፣ ስነ-ምግባር መር ውሳኔ ሰጭነትን፣ መልካም ባህሪ፣ ሰላም፣ መተባበር፣ ሌሎችን ማክበርና አርበኝነትን አካቷል። በአጠቃላይ ይህ ስርዓተ ትምህርት ተማሪዎች በጥልቅ ማሰብን፣ ችግር ፈቺና በሳል ውሳኔ መስጠትን የሚያስችሉ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ አተያይ እና እሴቶችን ያካተተ ነው።

# ማውጫ

ይዘት ገፅ

## ምዕራፍ አንድ

### የልጆች ራስን መግዛት


1.1 ራስንየመግዛት ምንነት ----------------------------------------1

1.2 ራስን የመግዛትቁልፍ ባህርያት ------------------------------------ 2

1.3 ራስንየመግዛትጠቀሜታ ------------------------------------------3

1.4 ራስን የመግዛት ማሻሻያ መንገዶች--------------------------------------5

1.5 የራስንደህንነት ከአካላዊ እና ስሜታዊ ጎጂ ተግባራት መጠበቅ ------5

1.6 ራስን ያለመግዛትውጤቶች ------------------------------------------6


## ምዕራፍ ሁለት

### የልጆች ስነ-ስርዓት በቤተሰብ ውስጥ


2.1 የቤተሰብ ምንነት ----------------------------------------------------9

2.2 የቤተሰብ አባላት ጠቀሜታ ---------------------------------------------10

2.3 በቤተሰብ ውስጥ የግብረ-ገብ እሴቶችና መርሆች -------------------------12

2.4 መልካም የቤተሰብ ግንኙነት -----------------------------------------13

2.5 መልካም የቤተሰብ ግንኙነትን የሚጎዱ ምክንያቶች -----------------13


## ምዕራፍ ሦስት

### ጉርብትና


3.1 የጉርብትናምንነት ----------------------------------------------------15

3.2 የመልካም ጎረቤቶች -------------------------------------------------16

3.3 የመልካም ጎረቤቶች ጠቀሜታ ባህሪያት ---------------------------------17

3.4 ከጎረቤቶች ጋር ያለ መልካም ግንኙነት ------------------------------18

3.5 መልካም ጉርብትናን የሚጎዱ ምክንያቶች ----------------------------19

# ምዕራፍ አራት

## የተማሪዎች ስነ-ስርዓት በትምህርት ቤት


4.1 የተማሪዎች ሰነ-ስርዓት በትምህርት ቤት ---------------------------------------22

4.2 የትምህርት ቤት ህጎችና ደንቦች ---------------------------------------23

4.3 በትምህርትቤት ውስጥ ያሉ የተማሪዎች መብቶችና ኃላፊነቶች -------------26

4.4 በትምህርት ቤት ውስጥ የሚታዩ መልካም ግንኙነቶች -------------------------28

4.5 በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ውስጥ በንቃት መሳተፍ --------------------29


# ምዕራፍ አምስት

## የማሕበረሰብ እሴቶችን ማወቅ


5.1 የማህበረሰብ ምንነት ---------------------------------------32

5.2 የማህበረሰብ እሴቶች---------------------------------------34

5.2.1 የማህበረሰብ እሴቶች ምንነት---------------------------------35

5.2.2 ዋና ዋናየማህበረሰብ እሴቶች ---------------------------------35

5.3 የማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታ ---------------------------------41


# ምዕራፍ ስድስት

## አካባቢያዊ ባህሎችን ማወቅ


6.1 የባህል ምንነት ---------------------------------------44

6.2 የአካባቢያዊ ባህል ምንነት---------------------------------------45

6.3 ዋና ዋና አካባቢያዊ ባህል አካላት ---------------------------------46

6.4 የአካባቢያዊ ባህል ጠቀሜታ ---------------------------------------47

6.5 የማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች ---------------------------------------49

# ምዕራፍ አንድ

## የልጆች ራስን መግዛት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማርውጤቶች፣ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የራስ መግዛት ምንነትንትገልፃላችሁ፡፡
- የራስ መግዛትየሚያሳዩቁልፍባህርያትንትገልፃላችሁ፡፡
- የራስ መግዛትአስፈላጊነትንዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡
- ራስንከአካላዊእናስሜታዊጎጂ ተግባራት ለመጠበቅጠቃሚ የሆኑልምዶችንታሳያላችሁ፡፡
- ራስን አለመግዛትየሚያስከትለውንውጤትትለያላችሁ።

## 1.1. ራስን የመግዛት ምንነት

ውድ ተማሪዎች፡-ራስን መግዛት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?

ራስን መግዛት የመልካም ባህሪ መገለጫ ነው። ይህ ማለት

የተከበረና የሚወደድ ሰው ሊኖረው የሚችል መልካም እና ተቀባይነት ያለው ባህሪ ነው ። የሚከተሉትን ነጥቦች በምሳሌነት ያካትታል ፡-

- ወላጆችንና ሌሎች የቤተሰብ አባላትን ማክበር
- ጤናማ ለመሆን የግል ንፅህናን መጠበቅ
- በተገቢው ሁኔታ ምግብን በአግባቡና በስርአቱ መመገብ
- አቅም በሚፈቅደው ልክ ቤተሰብን መርዳት
- በታማኝነትና በጥንቃቄ ጨዋታዎችን ከጓደኞች ጋር መጫወት ወዘተ።



ምስል1.1 ራሳቸውን የገዙ ልጆች የሚፈፅሟቸው ድርጊቶች

## 1.2. ራስን የመግዛት ቁልፍ ባህርያት

ውድ ተማሪዎች :- ራሱን የገዛ ሰው የሚከተሉት ባህርያት ያሉት

እንደሆነ አስታውሱ፡፡

- የራስን መግዛትህጎችንለማወቅይጓጓል
- ህጎችንምዕለትተዕለትይተገብራል
- የግብረ-ገብምርጫችግርሲገጥመውወላጆችንለመጠየቅድፍረትአለው
- መልካምባህሪንለመላበስየሌሎችንፈቃድአይጠይቅም፤
- ከቤተሰቡጋርሰላማዊግንኙነትአለው
- ከጎረቤቶቹምጋርሰላማዊግንኙነትአለው
- በትምህርትቤትውስጥታታሪተማሪነውወዘተ።



ምስል1.2ራሳቸውን የገዙ ልጆች ባህርያት

## 1.3. ራስን የመግዛት ጠቀሜታ

**ውድ ተማሪዎች** :-ራስን መግዛት በሚከተሉት የተለያዩ ምክንያቶች መሰረት ጠቃሚ ባህሪ ነው::ይህም ማለት ከአንድ ግለሰብ በላይ ማሕበረሰብን ስለሚረዳ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የሚከተሉት ሃሳቦች ራስን የመግዛት አስፈላጊነትን ያብራራሉ::

- ከተለያዩ አደጋዎች ነፃ ለመሆን
- ውጤታማ የማሕበረሰቡአባልለመሆን
- መልካምናውጤታማተማሪለመሆን
- በማህበረሰቡዘንድተወዳጅነትንለማትረፍ
- ሽልማትንለማግኘት
- በጓደኞች መካከል መልካምአርአያለመባልወዘተ::






ምስል 1.3 ራሳቸውን የገዙ ውጤታማ ልጆች

ውጤታማ ተማሪዎች አንድን ድርጊት ከመፈፀማቸው በፊት በጥልቀት ያስባሉ፡፡

ውጤታማ ተማሪዎች በሰሩት መልካም ስራ ሽልማትን ያገኛሉ፡፡

## 1.4. ራስን የመግዛት ማሻሻያ መንገዶች

**ውድ ተማሪዎች፡-ራስን መግዛት እጅግ አስፈላጊ ባህሪ በመሆኑ በተለያዩ መንገዶች መሻሻል እና ማደግ ይኖርበታል፡፡**

- ቀጣይነት ያለው የባህሪ ማሻሻልን መተግበር
- የወላጆችን ምክር ዘወትር መስማት
- አርአያ የሆኑ ግለሰቦችን ተግባር መለማመድ
- የግብረ-ገብ ትምህርትን ከእምነት ተቋማት መማር
- የእምነት መጽሐፍትን ማንበብ ወዘተ፡፡








ምስል 1.4ራሳቸውን የገዙ ልጆ

## 1.5.የራስን ደህንነት ከአካባዊ እና ስ

**ውድ ተማሪዎች፡-** ተገቢ የሆነ ራ
አካላዊ እና ስሜታዊ ጉዳቶች ሊደርስ
ሁለት ትረካዎች ይሄን ሃሳብ በተ

ትረካ 1:- ሀዋ እና ስንታየሁ በሐረር የሚኖሩ ጓደኛማቾች ናቸው። ሁለቱም 7 ዓመታቸው ነው። ከዕለታት አንድ ቀን ወላጆቻቸው ዘመድ ለመጠየቅ ሲሄዱ እጅግ የበዛ ስኳር ሰርቀው ቃሙ። ስኳሩ በጣም ብዙ ስለነበር ሁለቱም አመማቸው፤ ያስተውኩም ጀመር። ወላጆቻቸው ከሄዱበት ሲመለሱ ጥፋታቸውን አወቁና ለአንድ ሳምንት ሀዋ እና ስንታየሁ እንዳይገናኙ ቀጧቸው። ሁለቱም ለአንድ ሳምንት በብቸኝነትና በናፍቆት ተሰቃዩ።

ትረካ 2 :-፡-ሴና እና አልሚራህ በአዲስ አበባ የሚኖሩ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። አንድ ቀን ተደብቀው ለሁሉም ቤተሰባቸው የተዘጋጀውን የድንች ጥብስ(ችፕስ)በሙሉ በሉ።በዚህ ምክንያት ቀኑን ሙሉ ምግብ የመመገብ ፍላጎት አጡ።ከዚህ በተጨማሪ ወላጆቻቸው በተገቢው ሁኔታ ቀጧቸው።

ከዚህ በላይ በአነበባችሁት ሁለት ትረካዎች መሰረት በተገቢው ሁኔታ ራስን መግዛት ካልቻልን የአካልና የስሜት ጉዳት ይደርስብናል ። ስለዚህ ራሳችንን ከጎጂ ተግባራት ሁልግዜ መጠበቅ ይኖርብናል።.

## 1.6.ራስን ያለመግዛት ውጤቶች

**ውድተማሪዎች**:-ባለፈው የትምህርት ይዘት ራስን መግዛት የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ተምረናል፡፡ በዚህ ክፍል ራስን አለመግዛት የሚያስከትለውን ውጤት እንደሚከተለው በዝርዝር እናያለን፡፡

- የተለያዩ አካላዊ ጉዳቶች እንደ እሳት ቃጠሎ፣ የኤሌክትሪክ አደጋ እና መውደቅ መከሰት
- የስነ-ስርዓት መተላለፍ ቅጣቶችን ማስተናገድ
- በአካባቢ ጎረቤቶች ዘንድ እንደመልካም ልጅ አለመታየት
- አብሯችሁ የሚጫወቱ መልካም ጓደኞችን ማጣት
- ወላጆችን ማሳዘን እና
- ብቸኛ መሆን፡፡











ምስል 1.5 አደጋን የሚያስከትሉ አደገኛ የልጆች ድርጊቶች

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

**ራስን መግዛት፡-** በሰዎች የሚተገበር መልካም ባህሪ ነው፤ እንዲሁም መልካም የቤተሰብ ህይወት እንዲኖረንና ራስን ከማንኛውም አደጋለ መጠበቅ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

**ራሱን የገዛ ሰው፡-** የስነ-ስርዓት ደንቦችን ለመማር፣ ሰላማዊ ግንኙነትን ለማስፈን እና ቤተሰቡን ለማክበር ተነሳሽነት ያለውና የመልካም ባህሪ ባለቤት ነው።

**ራስን ያለመግዛት፡-** ለአካላዊና ስሜታዊ ጉዳቶች ያጋልጠናል፡፡

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ፡-**የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ።

1. ራስን መግዛት ሁልጊዜም በሌሎች አዛዥነት የሚፈፀም ነው።
2. ቤተሰብን ማክበር አንዱ ራስን የመግዛት አካል ነው።
3. ራስን መግዛት ከጎጂ ተግባራት አይጠብቀንም።
4. ሃይማኖታዊ መፅሐፍትን ማንበብ ራስ መግዛትን ለማሻሻል ይጠቅማል።
5. ራስ መግዛትን ለማሻሻል የተለያዩ መንገዶች አሉ።

# ምዕራፍ ሁለት

## የልጆች ስነ-ስርዓት በቤተሰብ ውስጥ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የቤተሰብን ፅንሰ ሃሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- የቤተሰብ አባላት ጠቀሜታ ታብራራላችሁ፡፡
- በቤተሰብ ውስጥ የሚተገበሩ የግብረ-ገብ እሴቶችንና መርሆዎችን ታሳያላችሁ፡፡
- በቤተሰብአባላትመካከልየሚደረጉመልካምግንኙነቶችንታ ደንቃላችሁ፡፡
- በቤተሰብ አባላት መካከል የሚደረጉ መልካም ግንኙነቶችን የሚጎዱ ምክንያቶችን ትለያላችሁ፡፡

### 2.1. የቤተሰብ ምንነት

**ውድ ተማሪዎች፡-** ቤተሰብ የሚለው ቃል በተለያዩ መንገዶች ፍቺ ሊሰጠው ይችላል፤ ቤተሰብ ማለት አብረው የሚኖሩ ማህበራዊ ቡድን ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ወላጆችን፣ ልጆችንና ቤተ-ዘመድን ያካተተ ቀዳሚ ማህበራዊ አካል ነው። እንዲሁም የቤተሰብ አባትን ፣ እናትን፣ሴት ልጅን፣ወንድ ልጅን፣ አክስትን ፣ አጎትን እና ሌሎችን ያካተተ አካልነው።



ምስል 2.1 ፋጡማ በባህር ዳር ቅድመ-አያቶቿን ስትጠይቅ

## 2.2 የቤተሰብ አባላት ጠቀሜታ

**ውድተማሪዎች፡-** ከምስሉ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ቤተሰብ የተለያዩ አባላትን ያካትታል።በመሆኑም እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እድሜውን ያገናዘበ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እና ድርሻ አለው።

**እናት፡-**የቤተሰብ መሪ ከሆኑት አንዷ ስትሆን በመሰረታዊነት የቤተሰቡን ምጣኔ-ሀብታዊ እና ማህበራዊ ግዴታዎችን ትተገብራለች።

**አባት፡-**ከቤተሰብ አባላት የመሪነት ሚና ሲኖረው፣ ቤተሰቡን በምጣኔ-ሀብት በመደገፍና ማህበራዊ ሚናን በመወጣት ያገለግላል፡፡

**ወንድ ልጅ፡-**አንዱ የቤተሰብ አባል ሲሆን፣ ቤተሰቡን፣ሌሎች የቤተሰብ አባላትን እንዲሁም ጎረቤቶቹን አቅሙ በፈቀደው ያገለግላል።

**ሴትልጅ፡-**እንደ ወንድ ልጅ ቤተሰብን ፣ሌሎች የቤተሰብ አባላትን እንዲሁም ጎረቤቶችን እያገለገለች ትምህርቷን በትጋት ትከታተላለች።

**አክስት**፣አጎት እና ሌሎች ቅርብ የቤተሰብ አባላት ቤተሰብ ነክ ጉዳዮችን ፣ምጣኔ-ሀብት እና ማህበራዊ ተግባራትን ከቤተሰብ ጋር ያከናውናሉ።

በአጠቃላይ የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ በደስታም ሆነ በችግር ወቅት መረዳዳት ይኖርበታል። በመሆኑም ሁሉም የቤተሰብ አባል በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው።

ትረካ1:-- ዮሃንስ ሀዋሳ በሚገኝ ልዩ ትምህርት ቤት የሚማር ተማሪ ነው::በትምህርቱም ምንም ዓይነት ችግርና ጭንቀት አይታይበትም ምክንያቱም ወላጆቹ ለትምህርት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁስና መሰል መሳሪያዎችን በተገቢው ሁኔታ ስለሚገዙለት ነው::

ትረካ 2:- ፋጡማ በደሴ ከተማ የምትኖር ተማሪ ናት::በመጪው ክረምት በጅግጅጋ ከተማ የሚኖሩትን ቅድመ አያቶቿን ለመጠየቅ ትሄዳለች:: ጉዞዋ የተሳካ እንዲሆንም አጎቷና እና አክስቷ የትራስፖርት ወጪዋን ለመሸፈን ቃል ገብተውላታል::

**በአጠቃላይ** ከሁለቱ ትረካዎች እንደምንረዳው የቤተሰብ አባላት በደስታም ሆነ በመከራ ወቅት ጠቀሜታቸው ከፍ ያለ ነው::



መልካም ጎረቤት የተጋጩ እናትና ሴት ልጅን ሲያስታርቅ



መልካም ጎረቤት በሃዘን ላይ ያለ ወንድ ልጅን ስታናግር

ምስል 2.2 የመልካም ጎረቤቶች ባህሪ

## 2.3. በቤተሰብ ህይወት ውስጥ የግብረ-ገብ እሴቶችና መርሆች

**ውድ ተማሪዎች:-** የግብረ-ገብ እሴቶችና መርሆች አንድ ድርጊት ወይም ባህሪ መልካም ተቀባይነትን የሚያሳዩ ህጎች ናቸው። የሚከተሉት ዝርዝር የግበረ-ገብ እሴቶችና መርሆች አንድ ቤተሰብ ሰላማዊ ህይወት እና በአግባቡ እንዲሰራ ይረዳሉ።

- በቤተሰብ አባላት መካከልመከባበርን ማስፈን
- በቤተሰብ ውስጥ የትብብር ስሜትን መፍጠር
- ፈጣሪን በመፍራትና በማሰብ ለቤተሰብ አባላት መታዘዝ
- የቤተሰብ የኑሮ ደረጃን በመረዳት ፣ በመተሳሰብ መኖር እና አቅም በሚፈቅደው ልክ ወላጆችንና የቤተሰብ አባላትን ማገልገል ወዘተ፡፡



ምስል 2.3 ውጤታማ የግብረ-ገብ እሴቶችንና መርሆችን የሚያከብር ቤተሰብ

## 2.4.መልካም የቤተሰብ ግንኙነት

ማንኛውም ቤተሰብ መልካም ግንኙነት ይኖረው ዘንድ እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ሊኖሩት ይገባል።

- ወላጆች እና ልጆች መልካም ባህሪ ሊኖራቸው ይገባል።
- ወላጆች እና ልጆች እርስ በእርስ መከባበር ይኖርባቸዋል።

ቴዎድሮስ እህቱ ትዕግስትና ወላጆቻቸው በጎንደር ከተማ ይኖራሉ። ወላጆቻቸው ለመኖር የሚያስፈልጓቸውን መሰረታዊ ቁሳቁሶች ያሟሉላቸዋል።ልጆችም ወላጆቻቸውን በጣም ያከብሯቸዋል።ከዚህ በተጨማሪ ልጆች አቅማቸው የሚችለውን የቤት ውስጥ ስራ ይሰራሉ። በመሆኑም ቤተሰባቸው መልካም ግንኙነት ስላለው ደስተኛ ነው።

## 2.5 መልካም የቤተሰብ ግንኙነትን የሚጎዱ ምክንያቶች

ውድ ተማሪዎች:-ቤተሰብ ለአንድ ሀገር ግንባታ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ መልካም ግንኙነት ን ለመፍጠር በአግባቡ ሊጠበቅና ሊመራ ይገባል።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች አንዳንድ ጊዜ በቤተሰብ መካከል መልካም ግንኙነት እንዳይኖር የሚያደርጉ ምክንያቶች ናቸው:-

- ትክክል ያልሆነ የቤተሰብ አስተዳደር
- ስነ-ስርዓትን የማያከብሩ ልጆች መገኘት
- የውጭ ሀገር ያልተገባ የባህል ጣልቃ ገብነት
- የሃይማኖት እና መሰል ተቋማት ሀላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት ወዘተ::

# የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

**ቤተሰብ፡-**የደም ትስስር ያላቸው የሰዎች ስብስብ ነው፡፡

**ሁሉም የቤተሰብ አባል፡-**በደስታም ሆነ በችግር ወቅት ይረዳዳል።

**መልካም የቤተሰብ እሴቶች፡-**ወላጆችን ማክበርና እርስ በእርስ መረዳዳትን ያካትታል፡፡

**መልካም የቤተሰብ ግንኙነት፡-**በምጣኔ-ሃብትም ሆነ በስነ-ልቦና የዳበረ ስብእናያስገኛል።

**መልካም ያልሆነ የቤተሰብ ግንኙነት፡-** ቤተሰብ ውስጥ አለመግባባትን በመፍጠር በርካታ ችግሮችን በቤተሰብ ላይ ያመጣል።

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ**:-የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ቤተሰብ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ አንዱየማህበረሰብ አካል ነው።
2. ቤተሰብ በደስታም ሆነ በችግር ወቅት ጠቃሚ ነው ።
3. ወላጆችን መርዳት አንዱ የቤተሰብ ግብረ-ገብ መርህ ነው።
4. መልካም የቤተሰብ ግንኙነት ጠቃሚ ነው።
5. መልካም የቤተሰብ ግንኙነት በተለያዩ ምክንያቶች ሊጎዳ ይችላል።

# ምዕራፍ ሦስት

# ጉርብትና

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የጉርብትና ምንነትን ትገልፃላችሁ፡፡
- የመልካም ጎረቤትን ጥቅም ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡
- የመልካም ጎረቤት ባህሪያትን ታሳያላችሁ፡፡
- መልካም ጎረቤቶችን ለመገንባት የውጤታማ ተግባቦት ሚናዎችን ትገልፃላችሁ፡፡
- መልካም ጉርብትናን የሚጎዱ ምክንያቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

## 3.1 የጉርብትና ምንነት

**ውድተማሪዎች፡-** የመልካም ጉርብትናን ምንነት ከመማራችሁ በፊት ጎረቤት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ይጠበቅባችኋል።

ጎረቤት ማለት ከምንኖርበት ቤት አቅራቢያ የሚገኝ ሌላ ቤት ወይም ቤተሰብ ነዉ፡፡

በአንድ አካባቢ የሚገኙ ጎረቤቶች እርስ በእርስ ሲረዳዱና ሲዋደዱ መልካም ጉርብትና ይባላል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ጠንካራ የሆኑ የመልካም ጉርብትና እሴቶች አሉን።በመሆኑም በደስታና በችግር ወቅት እርስ በእርስ እንረዳዳለን።ይህም መረዳዳት ምጣኔ-ሀብትን፣ ማህበራዊ ክንውንን፣ፀጥታ እና ደስታን ያካትታል።ልጆችም ወደ ሱቅ እና ገበያ በመሄድና ዕቃ በመግዛት እየተላላኩ ጎረቤቶቻቸውን ያገለግላሉ። ከዚህም በተጨማሪ ልጆች አብረው በመጫወት ማህበራዊህ ይወታቸውን ያጠናክሩበታል።

**ውድ ተማሪዎች** ከዚህ በፊት ለጎረቤቶቻችሁ ያደረጋችሁት መልካም ድርጊት ካለ ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡

### ሽምሱ እና ጎረቤቶቹ

ሽምሱበ ወልቂጤ ከተማ የሚኖር 1ኛ ክፍል የሚማር የ 7 ዓመት ልጅ ነው።እሱ መልካም የጉርብትና ባህሪያት አሉት። ከእነሽምሱ ቤት በስተግራ በኩል እማማ ፀሐይ ይኖራሉ።እማማ ፀሐይ እጅግ ያረጁ በመሆናቸው ሽምሱ ውሃ በመቅዳት እና በመላላክ ይረዳቸዋል።ከነ ሽምሱ ቤት በስተቀኝ በኩል የአስቴር ቤተሰቦች ይኖራሉ ።ሽምሱና አስቴር በተመሳሳይ እድሜና ክፍል ደረጃ ስለሚገኙ በመከባበርና በመተሳሰብ ከትምህርት ቤትና ከጥናት በኋላ ይጫወታሉ።እነዚህ ጎረቤቶች በስምምነት እና በህብረት የሚኖሩ ሰዎች ናቸው።ይህ ነው እንግዲህ መልካም ጉርብትና ማለት።

## 3.2 የመልካም ጎረቤቶች ባህሪያት

ውድተማሪዎች:-መልካም ጉርብትና እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነ ማህበራዊ እሴት ነው:: የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች መሠረት በማድረግ የመልካም ጎረቤቶችን ጠቀሜታ መረዳት ይቻላል ::መልካም ጎረቤቶች:-

- በደስታም ሆነ በችግር ወቅት ይረዳዳሉ::
- የሌሎች ጎረቤቶችን መብት በመገንዘብ በሰላምና በደስታይ ኖራሉ::
- አላስፈላጊ ጩኸትና ሁካታን በማስወገድ የሌሎች ጎረቤቶ ችን ሰላም በህመም ወይም በሌሎች ወቅቶች ይጠብቃሉ::
- የአካባቢን ንጽህና በመጠበቅ ምቹ የመኖሪያ አካባቢ እንዲፈ ጠር ይተጋሉ::

ከላይ የተገለፁት እና ሌሎች መሰል የመልካም ጎረቤት መገለጫዎች ማህበራዊ ህይወትን ምቹና ደስታ የተሞላበት ያደርጋሉ::



የመኖርያ አከባቢን በጋራ ማፅዳት



ጎረቤት ቤት ሲያድስ ወይም አጥር ሲያጥር ማገዝ

ምስል 3.1 በጎረቤታሞች መካካል ያለ መልካም ግንኙነት

## 3.3.የመልካም ጎረቤቶች ጠቀሜታ

**ውድተማሪዎች፡-**የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻውን ለረጅም ጊዜ ሊኖር አይችልም።ቤተሰባችን እጅግ እንደሚጠቅመን ሁሉ ጎረቤቶቻችንም በህይወታችን ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።ከሚከተሉት መሰረታዊ ነጥቦች አንጻር ጎረቤቶቻችን ጠቀሜታ አላቸው፡-

- ከቤተሰቦቻችንበመቀጠል ጎረቤቶቻችን ሁለተኛ የትምህርት ማግኛ መሰረቶች በመሆናቸው እኛን በመምከርና በማረም መልካም ማህበራዊ ስብዕና እንዲኖረን ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አላቸው።

- ቤተሰቦቻችሁ በስራም ሆነ በማህበራዊ ጉዳይ ቤት በማይገኙበት ወቅት ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ ያደረጋሉ፡፡
- ልጆቻቸውም አብረውን በመጫወት የደስታችን ምንጭ ናቸው፡፡
- የሥነ-ምግባር ጉድለት ካዩብን ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ለወላጆች በመስጠት ወደ ተስተካከለ ባህሪ እንድንመለስ ይረዱናል።
- የተሻሉ የትምህርት ቤት፣ሆስፒታል እና የስራ አማራጭን ለወላጆች በመጠቆም እንደ መጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ያገለግላሉ።
- ማህበራዊ ህይወታችን የዳበረና ውጤታማ እንዲሆን ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

## 3.4 ከጎረቤቶች ጋር ያለ መልካም ግንኙነት

**ውድተማሪዎች**፡-ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር በተለያዩ የህይወት ጉዟችን ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።በመሆኑም ከጎረቤቶቻችን ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት በመፍጠር ከሰዎች ጋር ያለንን የመግባቢያ ክህሎትን ማዳበር ያስፈልጋል።ከእነዚህ ክህሎቶች መካከል ጥቂቱ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡-

- ግልጽ የሆነ የመግባብያ ክህሎትን ማዳበር
- የሌሎችን ስሜት የመረዳት አቅምን ከፍ ማድረግ
- ስለሌሎች ሰዎች ስሜት ትኩረት እና እንክብካቤ መስጠት
- ነገሮችንከሌሎችሰዎችአስተሳሰብአንፃርመመልከት
- ሰዎች ችግር ሲገጥማቸው መርዳትና ማፅናናት
- ታማኝና ሀቀኛ ሰው መሆን
- ሰዎችን በትኩረትና በንቃት ማዳመጥ
- በቡድን ስራ ላይ እምነትን ማሳደር
- ችግር ፈቺ አስተሳሰብን መገንባት
- ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የተገለፁትን ከሰዎች ጋር ያለንን የመግባቢ ያክህሎቶችን በማዳበር ከጎረቤቶቻችን ጋር መልካም ግንኙነትን መፍጠር እና ህይወታችንን ደስተኛ ማድረግ ይቻላል።



እግር ኳስ የሚጫወቱ ሰላማዊ ልጆች

ምስል 3.2 በልጆች መካከል ያለ ሰላማዊ ግንኙነት

## 3.5.መልካም ጉርብትናን የሚጎዱ ምክንያቶች

**ውድተማሪዎች**:-ባለፈው የትምህርት ይዘት መልካም ጉርብትናን የተሻሉ የመግባቢያ ክህሎቶችን በመጠቀም እንዴት እንደምትመሰርቱ ተምራችኋል። በዚህ የትምህርት ይዘት ደግሞ መልካም ጉርብትናን የሚጎዱ ተግባራትን በዝርዝር ትማራላችሁ።

- አብዝቶ ብቸኛ መሆን
- ከአንድነትይልቅልዩነትላይትኩረትማድረግ
- የአልኮልናየዕፅተገዥነት
- የመግባባት ስብዕናን ማጣት
- ከማህበረሰብእሴት ጋርያልተሰማማሃሳብንማራመድ
- በህይወትላይጨለምተኛአስተሳሰብማዳበርወዘተ።

እነዚህ ከላይ የተገለፁት ነጥቦች መልካም ጉርብትና እንዳይኖር ምክንያት በመሆናቸው ከህይወት ልምምዳችን ልናስወግዳቸው ይገባል።



ምስል 3.3 አለመተባበር የሚያስከትለው አለመግባባት

## የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ

**ጎረቤት**:-ከምንኖርበት ቤት አጠገብ ወይም አቅራቢያ የሚገኝ ቤት ወይም ቤተሰብ ነው።

**ጎረቤቶቻችን**:-ከቤተሰባችን በመቀጠል ጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍል ናቸው።

**መልካም ጎረቤቶች**:-ግንኙነታቸውን ከፍ ለማድረግ የተሻለ የመግባባት ክህሎት ያዳብራሉ።

**መልካም ጉርብትናን የሚጎዱ**፡- ስነ-ስርዓት አልበኝነት እናመልካም ያልሆነ የውጭ አገር የባህል ጣልቃገብነት መልካም ጉርብትናን ሊያበላሹ ይችላሉ።

## የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

መመሪያ፣የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህትት ከሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ።.

1. መልካም ጉርብትና እና ጎረቤታማችነት ተመሳሳይ ሃሳብ ናቸው።
2. በትብብር ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ህይወት የመልካም ጉርብትና ባህሪ ነው፡፡
3. መልካም ጎረቤቶች በደስታም ሆነ በችግር ወቅት በጣም ይረዳዳሉ።
4. ውጤታማ የመግባቢያ ክህሎቶችን ማዳበር መልካም ጉረብትናን ለመፍጠር መሠረታዊና አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡
5. እጅግ የበዛ ብቸኝነት መልካም ጉርብትና እንዳይፈጠር ያደርጋል።

# ምዕራፍ አራት

## የተማሪዎች ሰነ-ስርዓት በትምህርት ቤት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች ሰነ-ስርዓት ምን ማለት እንደሆነ ታብራራላችሁ፡፡
- የትምርት ቤት ህጎችና ደንቦችን ትለያላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤት ውስጥ የሚታይ አስፈላጊና መልካም ግንኙነትን ትገልፃላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤት በሚገኙ ተጓዳኝ የትምህርት ተግባራት ውስጥ መሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ ትገነዘባላችሁ፡፡
- በክፍል ጓደኞቻችሁ መካከል ስላሉት መልካም ግንኙነቶች ታሳያላችሁ።

## 4.1 የተማሪዎች ሰነ-ስርዓት በትምህርት ቤት

**ቁልፍ ቃል፡- የክፍል ውስጥ ሰነ-ስርዓት**



ምስል 4.1 በአግባቡ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች

ተግባር 1: **ውድ ተማሪዎች**:-ከዚህ በላይ ያለውን ምስል ተመልከቱና ስለምን እንደሆነ ለመምህራችሁ ንገሩ::

1. በምስል 4.1 መሰረት የክፍል ውስጥ ስነ-ስርዓት ምን ማለት ነው?

የክፍል ውስጥ ስነ-ስርዓት ማለት የትምህርት ቤት ህግና ደንብን ማክበርና ማንኛውንም የመማር ማስተማር ሂደትን የሚጎዱ ድርጊቶችን ማስወገድን ይመለከታል::

## 4.2 የ ትምህርት ቤት ህጎችና ደንቦች

ተግባር 2: ጥንድ ጥንድ በመሆን ምስል 4.2 ምን እንደሚያሳይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሶቻችሁን ለመምህራቹ ተናገሩ



ምስል 4.2 በሰልፍ ስነስርዓት ወቅት የኢትዮጵያን ብሄራዊ መዝሙር የሚዘምሩ ተማሪዎች

በቡድን በመሆን በአብዛኛው በትምህርት ቤታችሁ የምታከብሯቸውን ህግና ደንቦች ከለያችሁ በኋላ መልሶቻችሁን ለመምራችሁ አብራሩ። ከዚህ በተጨማሪ የትምህር ትቤታችሁን ገፅታ የሚያሳይ ስእል ከሳላችሁ በኋላ የክፍል ህግና ደንቦችን በደንብ ፃፏቸው።የሰራችሁትን ለመምህራችሁ አሳዩ።

## መዝሙር 1

"ትምህርት ቤቴ ሁልጊዜ ያመራች ነች"

ትምህርት ስንጨርስ ስንወጣ እረፍት፣
በርትቼ ጠንክሬ ሥራ ለመሥራት፣
ተማመኑ በእኔ ቃሌን አደስኩት::

ቃልገባሁ ለራሴ ተገዢ ለመሆን ፣
አከብራለሁ ብየ ህግንና ደንብን፣
የምማርበትን የትምህርት ቤቴን፣
ሥርዓት ልከተል ግበረገብነትን፣
ራሴን አስከብሬ ለማክበር ሌሎችን::

## ግጥም

"ትምህርት ቤቴን እወዳታለሁ"

እክፍል ስገባ ዝቅ አድርጌ ራሴን ፣
ሠላም እላለሁኝ በክብር መምህሬን፣
ለመምህራንና ለክፍል ጓዶቼ፣
ትሁት ነኝ አክበሪ ሠላምታ ሰጥቼ፡፤

መምህራን ሲመክሩኝ ጠርተው በድንገት፣
የምሳማ ልጅ ነኝ ቆሜ ፊት ለፊት፣
በጥሞና እና በመረጋጋት ::

በመኝታ ክፍሌ አሳልፋለሁኝ፣
ወይንም ሜዳ ላይ እጨዎታለሁኝ፣
እረፍት የማርፍበት ጊዜ ካገኘሁኝ፣
ወጣ ብዬ መምጣት እፈልጋለሁኝ
ትምህርት ቤቴን ግን እወዳታለሁኝ



ምስል 4.3 ስነ ስርዓትን ጠብቀው በሰልፍ ወደ ክፍላቸው የሚገቡ ተማሪዎች



ምስል 4.4 ተማሪዎች መምህራቸው ወደ ክፍል ሲገቡ ቆመው ሲቀበሉ

## ተግባር 3፡ መመሪያ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት

ሀሰት ከሆነ ሐሰት በማለትመልሱ።

1. ሀላፊነት የሚሰማው ተማሪ የትምህርት ቤቱን ህግና ደንብ ያከብራል።
2. ክፍል ከመግባታችን በፊት የኢትዮጵያን ብሄራዊ መዝሙር መዘመር አላስፈላጊ ነው።
3. የትምህርት ቤት ህግና ደንብ ከሆኑት መካከል በሰዓት መገኘት አንዱ ነው።

## 4. 3 በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ የተማሪዎች መብቶችና እና ሀላፊነቶች



ምስል 4.5 ተማሪዎች የመማር መብታቸውን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ

ተግባር4: ከላይ በሚገኘው ምስል መሰረት ከታች ያሉትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ መልሱና ለመምህራችሁ አሳዩ::

1. ምስሉ ምንምን ያሳያል?

2.በምስሉ ላይ የምታይዋቸው ተማሪዎች ምን እያደረጉ ነው?

### መዝሙር 2

"ለትምህርት ቤቴ ቃል እገባለሁ!"

ግብረገብንና ሌሎች ትምህርቶችን፣
በርትቼ ላጠና ፈጽሞ ሳልባዝን፣

ቃል ገባሁ ለራሴ ጠንክሬ ልሥራ፤
መሰብሰብ እንድችል የውጤት አዝመራ፣
መብቴ ስለሆነ በፍሬው ልኮራ::

የትምህርት ቤቴን ህግ ለማክበር፣
ዩኒፎርሜን ልለብስ ላለማስቸገር፣
አሁንም ቃል ገባሁ ለመተባበር::

እርሳስ እስኪርቢቶ በሚገባ አሹዬ፣
ደብተሬንም ይዤ ለመማር ሆ ብዬ፣
ሄድኩኝ ት/ቤት መጽሐፍ አክዬ፣
መማር በመሆኑ ዋነኛው ሥራዬ፣

## 4.4 በትምህርት ቤት ውስጥ የሚታዩ መልካም ግንኙነቶች

ቁልፍቃል፡-መልካም ግንኙነት



ምስል 4.6 በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ተማሪዎች ሲወያዩ

ከዚህ በላይ የተገለፀውን ምስል ተመልከቱና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

**ተግባር 5.** ምስል 4.3 ምንም ንነገሮችን ያሳያል? በቡድን በመሆን በመካከላችሁ መልካም ግንኙነት የመፍጠርን ጠቀሜታ ተወያዩ፡፡

**ውድ ተማሪዎች፡-**በባህርያችሁ ሰው አክባሪ፣ ቀና፣ ሰው ወዳድ፣ታማኝ፣ ርህሩህ እና ተባባሪ ከሆናችሁ መልካምግንኙነትን ከክፍል ጓደኞቻችሁ አልፎ በትምህርት ቤታችሁ ከሚማሩ ሌሎች ተማሪዎች ጋር መፍጠር ትችላላችሁ::

ተግባር 6:-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት **ስተት** ከሆነ ሐሰት በማለት መልሱ።

1. ተማሪዎች በመካከላቸው መልካም ግንኙነት መፍጠር ይኖርባቸዋል።
2. ተማሪዎች ለክፍል ጓደኞቻቸው ተባባሪ መሆን የለባቸውም።
3. ሀቀኝነት አንዱ መልካም ግንኙነትን የምናዳብርበት መንገድ ነው።
4. እርስ በእርስ ስንደማመጥ መልካም ግንኙነትን መገንባት ይቻላል።
5. ቀናነት ለመልካም ግንኙነት መመስረት ምንም አስተዋጽየለውም።

## 4.5 በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት በንቃት መሳተፍ



ምሰል 4.7:- ተማሪዎች በትምህርት ቤት በሚካሄድ ክብረ በዓል ላይ በንቃት ሲሳተፉ

ተማሪዎች፤ከዚህ በላይ ያለው ምስል ምንን እንደሚገልፅ አብራሩ፡፡

በትምህርት ቤት በሚገኙ የስፖርት ክበብ፣ የድራማና ስነ-ፅሁፍ ክበብ፣ የበጎ አድራጎት ክበብ፣ የሙዚቃ ክበብ፣ የሂሳብ ክበብ እና የንባብ ክበብ መሳተፍ የተጓዳኝ ትምህርት (ክበባት) ተሳትፎ ይባላል።ድርጊቱም ከመደበኛው ዕለት ተዕለት ትምህርት አሰጣጥ በተለየ ሁኔታ ሊፈፀም ይችላል።

ተግባር 7:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ሀሰት ከሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ።

1. በትምህርት ቤት በሚገኙ ተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ላይ በንቃት መሳተፍ አስፈላጊ ነው።
2. የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት የመደበኛው የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት አካል ናቸዉ።
3. በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት በንቃት የሚሳተፉ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ይባላሉ።
4. የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ከመማሪያ ክፍል ውጪ ይከናወናሉ። በትምህርት ቤት በሚገኝ የሂሳብ ክበብ ላይ የላቀ ድረሻ በመውሰድ ተሳታፊ መሆን ማለት ነው።

## የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

**የትምህርት ቤት ህግና ደንብ፡-** በሰዓት ትምህርት ቤት መገኘትን፣ ዘውትር ንፁህ የደንብ ልብስ መልበስን፣ የኢትዮጲያ ብሄራዊ መዝሙር መዘምርን እና የትምህርት ቤት ንብረትን በተገቢው ሁኔታመጠበቅን ይመለከታል፡፡

**የክፍል ውስጥ ስነ-ስርዓት**:-የትምህርት ቤት ህግና ደንቦች ማክበርን ይመለከታል።

**የተማሪዎች መብት፡-**ትምህርት እና ምክርን ከመምህራን እና ከወላጆች የማግኘት መብት አላቸው።

**የተማሪዎች ሀላፊነት፡-**ሰዓትን አክብሮ መገኘት፣ለትምህርት ትኩረት መስጠት እና የደንብ ልብስን በተገቢ ሁኔታ ለብሶ መገኘትን ይመለከታል።

**መልካም ግንኙነት፡-**ሰው አክባሪነትን፣ ቀናነትን፣ ሃቀኝነትን እና ሰው ወዳድነትን ያካትታል።

**ንቁተሳትፎ፡-**በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ለምሳሌ እንደ ሒሳብ ክበብ፣ ምንባብ ክበብ እና ስነ-ጥበብ ክበብ ላይ የላቀ ድረሻ በመውሰድ ተሳታፊ መሆን ማለት ነው።

# የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

መመሪያ:- ከዚህ በላይ በተማራችሁት የትምህርት ይዘት መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ሐሰት በማለትመልሱ።

1. በትምህርት ቤት ውስጥ ተገቢ የሆነ ባህሪ ማሳየት አንዱ የትምህርት ቤት ስነ-ስርዓት ነው።
2. የትምህርት ሰዓትን አክብሮ መገኘት አንዱ የትምህርት ቤት ህግና ደንብ አካል ነው።
3. ሀላፊነት የሚሰማዉ ተማሪ የትምህርት ቤት ህግና ደንብን አይጥስም።
4. ሰዓትን አክብሮ መገኘት የአንድ ተማሪ ሀላፊነት አይደለም፡፡
5. የክፍል ጓደኞችን ማጻመጥ እና መረዳት መልካም ግንኙነትን ለመፍጠር ይጠቅማል።

# ምዕራፍ አምስት

## የማሕበረሰብ እሴቶችን ማወቅ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- ማህበረሰብ የሚለውን ቃል ምንነት ታብራራላችሁ፡፡
- የማህበረሰብ እሴቶች የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ታብራራላችሁ፡፡
- ቁልፍ የሆኑ የማህበረሰብ እሴቶችን ትለያላችሁ፡፡
- ለመልካም የማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታ አድናቆት ትሰጣላችሁ፡፡
- ዋና ዋና የማህበረሰብ እሴቶችን ታሳያላችሁ።

### 5.1 የማህበረሰብ ምንነት

**ቁልፍ ቃል፡-** አንድ ማህበረሰብ የተለያዩ የቤተሰብ፣ የጎሳ እና የሃማኖት ተከታዮችን አካቶ የያዘ ስብስብ ነው፡፡

ሮባ በአንድ መንደር የሚኖር ልጅ ነው፡፡ አባቱ ገበሬ ሲሆኑ እናቱ ደግሞ የቤት እመቤት ናቸው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ወላጆቹ የአጎቱ ልጅ ወደሚኖርበት ከተማ እንደሚወስዱት ቃል ገቡለት፡፡ በሚቀጥለው ቀን በማለዳ በመነሳት አውቶቡስ ተሳፍረው ወደ ከተማ መጓዝ ጀመሩ፡፡

አሚና አርብቶ አደር የማህበረስብ ክፍል በሚኖርበት አከባቢ ትኖራለች፡፡ ወላጆቿ በርካታ ግመሎችና ፍየሎች አሏቸው፡፡ አሚና ከአባቷ፣ ከእናቷ እና ከሁለት ወንድሞቿ ጋር አብራ ትኖራለች፡፡



ምስል 5.1 በገጠር የሚኖር የአርሶ አደር ማህበረሰብ



ምስል 5.2 የአርብቶ አደር ማህበረሰብ



ምስል 5.3 በከተማ የሚኖር ማህበረሰብ

ተግባር1፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ። ጥያቄዎቹ ከላይ የተሰጠውን ትረካ እና ምስሎችን መሰረት አያደርጉም፡፡

1. ሁሉም የማህበረሰብ አካል በገጠር ይገኛል፡፡
2. ማህበረሰብ ማለት ተነጣጥሎ የሚኖር የሰዎች ስብስብ ነው፡፡
3. በአነስተኛ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች እንደ የከተማ ማህበረሰብ አካል ይታያሉ፡፡
4. ገበሬዎች የገጠር የማህበረሰብ አካል ናቸው፡፡
5. በከተማ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩት አርብቶ አደር የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡

ተግባር 2፡ ውድ ተማሪዎች በቡድን በመሆን ስለ ማህበረሰብ ዓይነቶች ከተወያያችሁ በኋላ መልሶቻችሁን ለመምህራችሁአስረዱ፡፡

## 5.2 የማህበረሰብ እሴቶች

**ቁልፍ ቃል፡-የማህበረሰብ እሴቶች**



ምስል 5.4 እርስ በእርስ የሚከባበሩ ተማሪዎች

ተግባር 3፡ ውድ ተማሪዎች በቡድን በመሆን ከዚህ በላይ ያለውን ምስል በአግባቡ ከተወያያችሁበት በኋላ ምን እንደሚያሳይለ መምህራችሁ ንገሩ፡፡

## 5.2.1 የማህበረሰብ እሴቶች ምንነት

የማህበረሰብ እሴቶች ማለት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ አካላት የሚጋሩት አስተሳሰቦች ወይም እምነቶች ናቸው፡፡ መቻቻል፣መተባበር፣መከባበር፣ መረዳዳት እና መተሳሰብ ከብዙዎቹ የማህበረሰብ እሴቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ።

1. የማህበረሰብ እሴቶች ማለት የአንድ ማህበረሰብ አካላት በጋራ የሚያራምዱት እምነት ወይም አስተሳሰብ ናቸው፡፡
2. መከባበር ግለሰቦች የሚያዳብሩት የማህበረሰብ እሴት ነው፡፡
3. የማህበረሰብ እሴቶች በአንድ የማህበረሰብ አካል ለየብቻ የሚያራምዱት እምነት ወይም አስተሳሰብ ናቸው፡፡
4. መተባበር የማህበረሰብ እሴት አይደለም፡፡
5. መቻቻል የመልካም ማህበረሰብ እሴት መገለጫ ነው፡፡

## 5.2.2 ዋና ዋና የማህበረሰብ እሴቶች

መሰረታዊ የማህበረሰብ እሴቶች የአንድ ማህበረሰብ ቁልፍ የሆኑ

እምነቶችን እና ጸጋዎችን ያካትታሉ፡፡

ተግባር 5፡-የሚከተሉትን ምስሎች በመመልከት እያንዳንዱ ምስል ከሚወክለው ዋና ዋና የማህበረሰብ ዕሴቶች ጋር ራሳችሁን አስማሙ፡፡

1. መተባበር



ምስል 5.5 በመተባበር የሚያጠኑ ተማሪዎች

2. መቻቻል



ምስል 5.6 ተማሪዎች በመከባበር ሲጫወቱ

## 3. አካታችነት



ምስል 5.7 በመማርያ ክፍል የተተገበረ አካታች የመማር ማስተማር ሂደት

## 4. ትርጉም ያለው ተሳትፎ



ምስል 5.8 ተማሪዎች በትምህርት ቤት ግቢያቸው በንቃት አትክልት ሲንከባከቡ

## 5. መከባበር



ምስል 5.9 ተማሪዎች የተቀመጡበትን መቀመጫ ለታላላቆቻቸው በመልቀቅ መከባበርን ሲገልፁ

## 6.እንግዳ ተቀባይነት



ምስል 5.10 ወላጆች ከትምህርት ቤት የሚመለሱ ልጆቻቸውን በፍቅር ሲቀበሉ

## 7. ቅንነት



ምስል 5.11ተማሪዎች በቅንነት የመማር ማስተማር ሂደትን ሲያከናውኑ

## 8. የሌላውን ሃሳብ መቀበል



ምስል 5.12 ልጆች በቀና መንፈስ በመደማመጥ ሲወያዩ

## 9. ተስፋ



ምስል 5.13 ለተሻለ ነገ የምትተጋ ታዳጊ

## 5.3 የማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታ

**ቁልፍ ቃል፡-** የማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታ

**ውድ ተማሪዎች፡-** ባለፈው የትምህርት ይዘት ስለማህበረሰብ እሴቶች ምንነት ተምራችኋል፤ በዚህ የትምህርት ይዘት የማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታን ትማራላችሁ። የሚከተሉት ዝርዝር ሃሳቦች የማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታን በጥልቀት ያመለክታሉ፡-

- ባህሪን በአግባቡ እንድንቆጣጠር እና እንድንመራ
- ልዩነትንና ብዝኀነትን ለመረዳት
- ከሌሎች ጋር በመተባበር ለመስራት
- ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለመስጠት እና
- ለተቀረው የማህበረሰብ አካል ሀቀኛና አክባሪ እንድንሆን ይረዳል።

**ተግባር 6፡-** በቡድን በመሆን የማህበረሰብ እሴቶችን ጠቀሜታ ከተወያየችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡




ምስል 5.14 አራቱ መሰረታዊ የማህበረሰብ እሴቶች

ተግባር 7:- የሚከተሉትን ጥያቄዎችከላይ ባለው የምልክት መግለጫ መሠረት መልሱ::

1. በመግለጫው ላይ የሚገኙት አራቱ ምልክቶች ምን ምንን ይወክላሉ?
2. በመግለጫው ላይ የሚገኙ ምልክቶች ከማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታ አንፃር ምንን ያሳያሉ?

## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

**ማህበረሰብ፡-** በአንድ አካባቢ በጋራ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል።

**የማህበረሰብ አካላት፡-**በገጠር የሚኖሩ፣በከተማየሚኖሩ፣አርብቶአደር፣አርሶአደርእናበሃይማኖትየተደራጁሊሆኑይችላሉ።

**የማህበረሰብእሴቶች፡-** በአንድማህበረሰብበጋራየሚራመዱአስተሳሰብወይምእምነትናቸው.

**ቁልፍ የማህበረሰብ እሴቶች፡-**ትርጉምያለውተሳትፎ፣መከባበር፣መተባበር፣ቅንነት፣መረዳዳት፣መቻቻልእናመተሳሰብንያካትታል።.

**የማህበረሰብ እሴቶችጠቀሜታ፡-**ባህሪንለመቆጣጠር፣ልዩነትንለማጣጣም፣የትብብርመንፈስንለመፍጠር፣ብቁየሆነውሳኔለመስጠትእናሀቀኛባህሪንማዳበርእንደምሳሌሊወሰዱይችላሉ።

# የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ተግባር ሁ፡በዚህ ምዕራፍ በተማራችሁት መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ሐሰት በማለት ፃፉ።

1. በከተማ የሚኖሩ ሰዎች የገጠር ማህበረሰብ አካል ናቸው
2. መረዳዳት ማለት አብሮ መስራትና መደጋገፍን ያመላክታል።
3. ለባንዲራ ከፍ ያለ አክብሮት መስጠት ከመከባበር ጋር ሊዛመድ ይችላል።
4. ገበሬዎች በገጠር ማህበረሰብ ውስጥ ይካተታሉ፡፡
5. ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የማህበረሰብ እሴቶች ይጠቅማሉ።

## የቃላት ስብስብ

**የማህበረሰብ እሴቶች, ማህበረሰብ እሴቶች ጠቀሜታ, ማህበረሰብ ከተማ ማህበረሰብ, ቅንነት**

1. በአንድ አካባቢ ተሰባስበው የሚኖሩ ሰዎች ——— ይባላሉ።
2. የአንድ ትልቅ ከተማ ነዋሪዎች የ ____________ ሊባሉ ይችላሉ።
3. ትክክል የሆነን ነገር ብቻ መስራት ______________ ይባላል።
4. የሰዎች የጋራ የሆኑ እምነቶችን ማራመድ ——— ይባላል።
5. ለተቀረው የማህበረሰብ አካል ክብርን መስጠት የ______________ መገለጫሊሆንይችላል።

# ምዕራፍ ስድስት

## አካባቢያዊ ባህሎችን ማወቅ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- ባህል የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ ታብራራላችሁ፡፡
- የአካባቢያዊ ባህል ምንነትን ታስረዳላችሁ፡፡
- ዋና ዋና የአካባቢያዊ ባህሎችን ትዘረዝራላሁ፡፡
- የራሳችሁን ባህል ታደንቃላችሁ፡፡
- የማህበረሰባችሁን ባህላዊ እሴቶች ታሳያላችሁ።
- መርህ ማለት መሪ ሃሳብ ማለት ነው ።
- ወግ ማለት ስርአተ ደንብ ነው።

## 6.1 የባህል ምንነት

ቁልፍ ቃል:- ባህል

ባህል ማለት የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ የሚያሳይ ነው።ይህም ክንውን በቃል ወይም በጽሁፍ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ሊሸጋገር ይችላል ። ሰዎች ባህላቸውን በሙዚቃ፣ በሃይማኖት፣ በአልባሳት፣ ምግቦችን እና ሌሎች ድርጊቶችን በመጠቀም ሊያንፀባርቁ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ የሰዎች ባህል በወግ እና ልማድ ላይ የተመሰረተም ነው።

ተግባር 1:-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

1 ባህል ማለት ምንድ ነው?

2. ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት ይሸጋገራል?



ምስል 6.1 የሀገር ሽማግሌው ስለ ባህላቸውና ወጋቸው ትረካ ሲተርክ

ተግባር 2፡-ከዚህ በላይ ያለውን ምስል በቡድን በአግባቡ ከተረዳችሁ በኋላ ምስሉ ስለ ምን እንደሆነ ለመምህራችሁ አስረዱ።

## 6.2 የአካባቢያዊ ባህል ምንነት

የአካባቢያዊ ባህል ማለት በመኖሪያ አካባቢያችን ዕለት ተዕለት የምንፈፅማቸውን ድርጊቶች ያመለክታል።



ምስል 6.2 የሐመር ብሂረሰብ አባላት ባህላቸውን ሲገልፁ

ተግባር 3፡-ከዚህ በላይ ያለውን ጽሁፍ እና ምስል በመረዳት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የአካባቢያዊ ባህል ምን ማለት ነው?
2. ምስሎቹ ስለ ነዋሪዎቹ አካባቢ ባህል ምን ያስረዳሉ?
3. በምስሎቹ የሚታዩ ሰዎች ምን የጋራ ነገር አላቸው?

በአካባቢያችሁ ከሚኖሩ ነዋሪዎች የምትጋሯቸውን ሦስት ልማዶ ችግለፁ?

## 6.3 ዋና ዋና አካባቢያዊ ባህል አካላት

**ቁልፍ ቃል**:-ዋና ዋና የአካባቢያዊ ባህል አካላት



ምስል 6.3 ተማሪዎች ከክፍል ወጪ ሲወያዩ



ምስል 6.4 ሰዎች የተለያዩ ባህላዊ ቁሳቁሶችን የያዘ ቤተ መዘክር ሲጎበኙ



ምስል 6.5 የሙዚቃ ባለሙያዎች ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎችን ሲጫወቱ

ቋንቋ፣ ምልክቶች፣ ልማዶች፣ እሴቶች፣ አልባሳት፣ ሙዚቃዎች፣ ምግቦች እና እምነቶች ዋና ዋና የአካባቢ ባህል አካላት ናቸው።

ተግባር4፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በላይ በተገለጹት ምስሎች በመታገዝ መልሱ፡፡

1. ዋና ዋና የአካባቢ ባህል አካላት ምን ምን ናቸው?

በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ የሚገኙ ዋና ዋና የአካባቢ ባህል አካላትን ከለያችሁ በኋላ ለመምራችሁ አስረዱ፡፡

## 6.4 የአካባቢያዊ ባህል ጠቀሜታ

**ቁልፍ ቃል፣**የአካባቢያዊ ባህል ጠቀሜታ

የአካባቢያዊ ባህል በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡-ማህበራዊና ምጣኔ ሀብትን ለማበልፀግ፣ የህይወት ሂደትን ለማሻሻል ፣ከሌሎች የማህበረሰብ አካላት ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ፣ታጋሽነትን ለማዳበር እና አጠቃላይ የማህበረሰብ ደህንነትን ለመመስረት ይረዳል።



ምስል 6.6 አብሮ የሚኖሩ የማህበረሰብ አካላት ሲወያዩ



ምስል 6.7 የማህበረሰብ አባላት እርስ በእርስ ሲረዳዱ



ምስል 6.8 ወንድ ልጅ ወደቀች ሴት ልጅን ለማንሳት ሲሞክር

ተግባር5፡-የሚከተለውን ጥያቄ ከላይ በሚገኘው ምስል መሰረት መልሱ፡፡

በቡድን በመሆን የአካባቢ ባህል ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ከተወያያችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አስረዱ( አብራሩ)።.

## 6.5 የማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች

**ቁልፍቃል፡- ባህላዊ እሴቶች**

ባህላዊ እሴቶች አጠቃላይ የማህበረሰብ መርሆዎች እና እሳቤዎች የሚመሰረቱበት ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው።.

ተግባር 6፡-የሚከተለውን ጥያቄ ከላይ ባለው ጽሁፍ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን መልሱ፡፡

ባህላዊ እሴቶች ማለት ምን ማለት ነው?

## ምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

ባህል:-የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ ያሳያል።

**የባህል መገለጫዎች**:- ሙዚቃ ፣ ሃይማኖት፣ አልባሳት፣ ምግቦች እና ሌሎች ድርጊቶች እንደምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ።

የአካባቢያዊ ባህል:- በመኖርያ አካባቢያችን ዕለት ተዕለት የምንፈጽማቸውን ድርጊቶች ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪም በጋራ የሚፈፀሙ ልማዶችን እና ደንቦችን ያካትታል ። አካባቢያዊ ባህል የተሻለ ህይወት እና መቻቻል እንዲሰፍን ይረዳል፡፡

የአካባቢያዊ ባህል አካላት:-ቋንቋ፣ ምልክቶች፣ ልማዶች፣ እሴቶች እና ቁሳቁሶችን ያካትታል።

የማህበረሰብባህላ ዊእሴቶች:-በአንድ ማህበረሰብ መርሆዎች እና እሳቤዎች የሚዳብር ክንዋኔ ነው።

## የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ተግባር ሀ፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በተማራችሁት መሰረት ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ባህል ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ሊሸጋገር የሚችለው በፅሁፍ ብቻ ነው።
2. ወጎች እና እምነቶች የባህል መሠረት ናቸው።
3. በአንድ ማህበረሰብ የሚኖሩ ሰዎች የጋራ የሆነ የአካባቢ ባህል ተሞክሮ ሊኖራቸው ይችላል።
4. የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ እርስ በርስ መቻቻል የለባቸውም።
5. ሃይማኖታዊ የበዓል ስነ-ስርዓቶች ልማድ ናቸው፡፡

ተግባር ለ፡-ዋና ዋና የአካባቢ ባህል አካላትን ዘርዝሩ፡፡

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________